# ሀገራቺን በውጪ ከሚኖሩ የምትጠብቀው።

## ይህ ጥንቅር እ.ኢ.አ በ 1994 ዓ.ም የቀረበ ቢሆንም፤አሁንም ለአንባቢያንና ለአድማጮች ቢቀርብ ጠቀሜታ አለውና ብትከታተሉት መልካም ነው።

ሐዲስ ለማ /ከጀርመን/

በነጻነቷ ታፍራና ተከብራ ለመቆየቷ ታሪክ የሚመሰክርላት ውድ እናት ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ልጆችዋ በኢትዮጵያዊነታቸው ኮርተውና ተከብረው እንዳልነበሩ፤በተፈጥሮአዊ አቀማመጧና ሀብቶቹዋ፤ በባሕላዊ ቅርሶቿ በአየር ጸባዮቿዋ በዓለም አደባባይ ተሰሚነት በነበራቸው ልጆቿ በእንግዳ አቀባበሉዋና የአፍሪካ መዲና በመሆንዋ ብቻ ሳይሆን፤የመጀመሪያው የሰው ልጅ ቅሬተ አካል የተገኘባት ሐገር፡መሆኗ በተመራ ማሪዎች ይፋ፡ሆኖ የተለያዩ ባለሙያዎችን፡የታሪክ፡ዐዋቂዎችን የበርካታ ቱሪስቶችንና፡የዓለም፡ህብረተሰብን ልዩ፡ትኩረት ስቦ፡እንዳልነበረ ድንበሩዋን ለመድፈር አንድነቷን ለማናጋትና ነጻነቷን፡ለመግፈፍ በየጊዜው ተነስተውባት፡የነበሩትን የውጭ ኃይሎች በልጆቹዋ፡ህብረት አልደፈርባይነትና መስዋዕትነት እያሳፈረች እንዳልመለሰችና ለሌሎችም፡በተለይ፡ለጥቁር ሕዝቦች ጥሩ አርያና መመኪያ ሆና እንዳልታየች ሁሉ፤ዛሬ ባለባት ፖለቲካዊ፡ኢኮኖሚያዊና፡ማህበራዊ፡ችግሮች፡ላይ፡ተፈጥሮአዊ፡ችግር፡ታክሎበት፡ሕዝቧ በገዛ፡ሀገሩ በሰላም፡ለመኖር ዋስትና፡ያጣበት ብቻ፡ሳይሆን፡ለአስከፊ፡ድህነት፡ለችግር፡ለርሃብና ለተለያዩ፡ቀሳፊ በሽታዎች ተጋልጦ ያለበት፤ ዕፅዋት በአየር፡ፀባይ መዛባት፡እንዲሁም፡ተገቢውን፡ ክትትል፤እንክብካቤና፡ጥበቃ ባለማግኘት፤ ልምላሜአቸውን፡እያጡ የሚደርቁበትና፡በሰደድ፡እሳት፡የሚጋዩበት፤ የዱር አራዊትና፤አዕዋፍም ሕይወታቸውን፡ለማቆየት፡ወደሚችሉበት፡አካባቢ እንደሰው፡እንዲሰደዱ፡የሚገፋፏቸው መጥፎ፡አዝማሚያዎች የሚታዩባት ብቻ ሳትሆን፡የአንድ፡ሀገር፡ልጆች፡በተለያዩ ምክንያቶች ለተለያዩ ምክንያቶች በየጊዜው ጦርነት፡የሚያካሂዱባትና የብዙ ሺ.ህ፡ወድሞቻችንና፡እህቶቻችን፡ሕይወት የሚጠፋበት፤ለልማትና ለሀገር ዕድገት፡የሚውል በርካታ የሀገር፡ሀብት ያለአግባብ፡የሚባክንባት ያልታደለች፡ሀገር፡መሆኗ፡እንኩዋን፡ለእኛ ለኢትዮጵያውያን፡ለባዕድም የአደባባይ፡ሚስጥር ከሆነ ውሎ አድሯል።ታዲያ፡በሰው፡ሰራሽና በተፈጥሮ ችግር ሳቢያ፡እንደቅጠል የሚረግፉ፡ወገኖቹን ሰቆቃና ስቃይ እያየነ እየሰማ የሰላም እንቅልፍ የሚተኛው ማነው፤ሰባዐዊነት የሚሰማው ዜጋ፤ማነው፡ እሱ ወንድማማቾች ጦር ተማዘው ደም ሲፋሰሱ፤እርስበርስ ሲጨፋጨፉና ሲተላለቁ እያየ ደስተኛ የሚሆነው፤የወለደች እናት፤ማነው እሱ ከዚህ አሰቃቂ ድርጊትና ድራማ የሚያተርፈው፤ሀገርና ሕዝብ፤ ለጥያቄዎቹ መልስ ከሁላችንም ስለሚጠበቅ ወደዝርዝር ነጥብ አልገባም።በእርግጥ ተምረው ለችግሮቻችን መፍትሔዎች ይፈልጋሉ፤ለሀገራችንም ዕድገትና ሰላም ያምጣሉ፤ለኛም፤ መመኪያ ይሆናሉ፤ብሎ ሳይማር፡ያስተማረንና በአሁኑ፡ጊዜ በችግር፡አለንጋ፡እየተገረፈ ችግሩን፡ስቃዩን፡ብሶቱን፡በደሉንና፡እሮሮውን፡የሚሰማውና፡በዚህ፡ቀውጢ ጊዜ ደራሽ ያጣውን ወገናችንን ማሰቡና ዐቅም ችሎታና ሁኔታ፡እንደፈቀደ አለንልህ፡ማለቱ ተስፋው፡እንዳይጨልም፤የሕልውና ዋስትናው እንዳይደበዝዝ፡፤የመኖር ትርጉምን ተግባራዊ፡እንዲያደርግ የሚያበረክተው፡አስተዋፆኦ ቀላል አይደለም። በሌላ፡በኩል፡ደግሞ በሀገሪቱ፡ላይ ተንሰራፍተው፡የሚገኙ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ተዛማች ችግሮችን፡ብቻ፡ሳይሆን፡አስከፊውን፡የርስበርስ፡መተላለቅ ሊያስከትሉ ይችላሉ ተብለው የሚፈሩ መጥፎ አዝማሚያዎችን፡ለማስቀረትና፡ከወዲሁ፡ለመቅጨት፤ከምንጊዜውም በላይ አሳሳቢ እየሆነ በመጣውየአንድነት ጥያቄ፡ላይ፡ከኛ ከኢትዮጵያውያን፡ምን፡ይጠበቃል፤የሚለውን ጥያቄ ማንሳቱ ወቅታዊና ተገቢም በመሆኑ፤ ለጥያቄው፡ምላሽ፡ለመስጠት፡የሕሊና፡ዝግጅት፡ማድረግ፤ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን በተላበሰና ምሁራዊ ለዛና ቃና ባለው መልኩ ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጥ፤መወያየት መቀራረብ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የጋራ መድረክ ማዘጋጀት አሌ የማይባል ሐቅ ነው።

ስለዚህ በዚህ ወሳኝና ሀገራችንና ወገኖቻችን የሰው ያለህ የወገን ያለህ እያሉ በሚጣሩበት ጊዜ የጎን ታዛቢዎች ሳንሆን፤ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ለተለያዩ ምክንያቶች ሲሉ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከፋፍሉንና ሊያዳክሙን ለሚፈልጉ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ጆሮና ልብ ሳንሰጥ ህብረታችንንና አንድነታችንን በመጠበቅና በማጠናከር ለኢትዮጵያዊነት ተመልሶ ማበብና መፋፋት፤ለጥሩ ትሩው ባህላችን ማደግና መስፋፋት ለሀገራችን በጥሩ ስም መጠራት፤ለወገኖቻችን አስከፊ ችግር መቀረፍ፤የበኩላችንን ማድረግ እንዳለብን ከሌሎች ሊነገረን የሚገባና በለሆሳስ የምናልፈው ቀላል ጉዳይ ሳይሆን፤ወቅቱና እውነታው አስገድዶን በተግባር ልንገልጸው የሚገባ ዐቢይ ጉዳይ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው።

ህብረታችንን አንድነታችንንና ኢትዮጵያዊነትን በመፈታተን እኛን የአንድ ሀገር ልጆች ለመለያየት ለመከፋፈልና የጎሪጥ እንድንተያይ፣በነገር እንድንወጋጋና እርስ በርስ እንድንቦጫጨቅ፣የስነልቦናና የጭንቀት ተጠቂዎች እንድንሆን ብቻ ሳይሆን፣እርስ በርስ ለመተላለቅ የሚያዘጋጁ መጥፎ አዝማሚያዎችንና ተግባራዊ እየሆኑ ያሉትን ተንኮል አዘል ዘዴዎች መጥቀሱ ለቀባሪው ማርዳት እንዳይሆንብኝ በመስጋት ብቻ ሳይሆን፣ዘዴዎቹ ከምንገኝበት ጊዜና ከዓለም ህብረተሰብ ዕድገት ጋር ሊጣጣሙ የማይችሉ፣ሁዋላ ቀር፣አሳፋሪ፣የህብረትና የአንድነት፣የሰላምና የዕድገት እንቅፋትና የህብረተሰብ ነቀርሳ በመሆናቸው፣እንኳዋን በተግባር መተርጎሙ በአነጋገር ደረጃም ሆነ በጽሁፍ ውስጥ መጥቀሱ ጤናማ መስሎ ስለማይታየኝ፣በማለፍ፣ አንድ በዚህ አጋጣሚ ሳልጠቅሰው የማላልፈው ነጥብ፣ የሌሎች መሰረታዊ መብቶችን ለመጋፋትና ለመርገጥ መሞከሩ፣ በግል ሕይወት፣ስሜትና ነጻነት ውስጥ ጣልቃ እየገቡ መተናኮሉ ትዝብት ከማትረፉ በስተቀር፣ለጤናማ ማህበራዊ ግንኙነት፣ለመተሳሰብ ለመቀራረብ ለመረዳዳት ለመደጋገፍ፣ህብረታችንንና አንድነታችንን ለማጠናከር፣እንዲሁም ለኢትዮጵያዊነት ማበብና መጎልበት የሚያበረክተው ቅንጣት አስተዋጽዎ የሌለ መሆኑን ነው።ለኔ እንደሚገባኝና እንደማምንበት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከጡት ነካሾች በስተቀር የእናት ሀገሩ የደስታዋም ሆነ የችግሩዋ ቀጥተኛ ተካፋይ መሆን ስላለበት በዚህ ውስብስብና አስቸጋሪ ወቅት የዜግነትና የትውልድ ግዴታውን ለመወጣት የሌሎችን መብትና ንጻነት ስይነካ ወይም ሳይጋፋ ሊከበሩ የሚገባቸውን የሰው ልጅ መብቶች እያከበረ፣ ለወገንና ለሀገር የሚበጀውን ለማድረግ የበኩሉን ጥረት ማድረግ እንዳለበት ነው።ይህም አንጻራዊ በሆነ አነጋገር እኛ ከሀገራችን ውጪ የምንኖር ኢትዮጵያውያን አስከፊውን የስደትና የባዕድ ሀገር ኑሮ ሳንዘነጋ ማለት ነው፣ ሀገር ቤት የስቃይና የሰቆቃ ኑሮ ከሚኖረው ወገናችን ሻል ያለ ኑሮ ስለምንኖር በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር ለርሃብና ለበሽታ የተጋለጡ ወገኖቻችንን መርዳት የምንችልበትን ዘዴዎች በጋራ እየቀየስን ለተግባራዊነቱም በጋራ መንቀሳቀስ፣የመበቀል የመናናቅና እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ የሚለውን ሁዋላ ቀርና ግለኛ አስተሳሰብ በመተው ችግሮቻችን በውይይት በተለይም የችግሩ ተጠቂ በሆነው አካል እውነተኛ ተወካዮች ተሳትፎ ሊፈቱ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት፣በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ኃይልን፣ህብረትን፣ጥንካሬንና አንድነትን ለማናጋት የሚጥሩ ኃይሎች መጠቀሚያ ላለመሆን መጠንቀቅ፣ለፕሮፓጋንዳ ሥራና ለጥቅም ሲሉ ከእዉነት የራቀና አንዱን ከአንዱ ሊያጋጭ የሚችል ሥነምግባር የጎደለው ዜና የሚያሰራጬትንና በማር የተጠቀለለ መርዝ ለማጉረስ የሚከጅሉ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችንም ሆነ የዜና ማሰራጫዎችን ማንነት ጠንቅቆ ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ከመጥፎ ድርጊታቸው ሊታቀቡ የሚችሉበትን ትምህርት ሰጪ እርምጃ መውሰድ ባጠቃላይ የሀገራችንንና የወገኖቻችንን አንገብጋቢ ጉዳይ ምንተዳዬ በማለት ለጥቂቶች ሳንተው፣ በሕዝብና በሀገር ስም ሕዝብና ሀገርን የሚጎዳ ስራ እንዳይሰራ፣የሕዝብና የሀገር ጠበቃ መሆንንና፣ሕዝባዊና ሀገራዊ አጀንዳ ይዘው የሚንቀሳቀሱ አካሎችም፣ተባብረው ለሕዝብና ለሀገር የሚጠቅም ማለትም ተስፋ ከሚሰጡ ፕሮግራሞችና መግለጫዎች በተጨማሪ ሕዝብን ከጎን ሊያሰልፍ የሚችል ጎልቶ የሚታይ ስራ እንዲሰራ ግፊት ማድረግን፣ ጠቅለል ባለ መልኩ በሀገራችን፣በሕዝባችንና በኛም በእራሳችን ዕጣ ፋንታ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንድንሆን ወቅቱ ይጋብዘናል።

ምን ጊዜም ቢሆን ኢትዮጵያዊነታችን ክብራችንና ጌጣችን፣ህብረታችንና አንድነታችን ደግሞ ኃይላችንና ጥንካሬአችን መሆኑን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሰው ሰራሽ ችግር ሳታጣ እንድታጣ ተደርጋ፣ የድርቅ የርሃብና የችግርተኞች ምሳሌና የዳቦ ተመጽዋች የሆነቺው እናት ሀገራችን የምትገኝበትን ሁኔታ ከእኛ ከልጆቹዋ የተሻለ ሊያውቅና ሊደርስላት የሚችል እንደሌለ ተገንዝበን፣የሀገራችንን፣ የአህጉራችንን፣የምንኖርበትን አካባቢና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን በስሜት ብቻ ሳይሆን በጥልቀት በማጤን ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የሚበጀውን ልናደርግ የምንችልበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት እንዳለብን ወቅቱ ከእኛ የሚጠብቀው የውዴታ ግዴታ ስለሆነ፣እነዚህን ተደራራቢ ተለዕኮዎች በአግባቡ ለመወጣት በየአካባቢያችን በሚገኙ ኮሚኒቲዎች ሥር መሰባሰቡና ኮሚኒቲዎቹ ዕቅዶቻቸውንና ዓላማዎቻቸውን ከግብ እንዲያደርሱ ማገዝ ጥሩ አማራጭ ነው።

መቼም መሸቶ መንጋቱ እንደማይቀር ሁሉ ፍቅርና እውነታ በጥላቻና ከእውንውት በራቁ አፍራሽ ክስተቶች ላይ አሸናፊ መሆናቸው የማይታበል ሐቅ ነውና የሀገራችን፣የወገኖቻችንና የራሳችንም ችግሮች ሊቃለሉ ይችሉ ዘንድ፣በእውነት ለእውነት ድምፃችንን እያሰማን፣የግል ጥቅምንና ፍላጎትን በሌሎች መጎዳት ለማሙዋላት የሚደረገው መሩዋሩዋጥ ውሎ አድሮ የሚያስከትለውን መዘዝም ከወዲሁ በመገንዘብ፣ዕቅማችን፣ችሎታችንና የጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ የፈቀደውን ለማድረግ ብንጥር፣ሌላው ቢቀር ከዘወትር የህሊና ወቀሳና ፀፀት ትንሽ እፎይ እንደምንል ጥርጥር የለውም።

ከዚህ ውጪ በትንሽ በትልቁ ሕዝብ ማለትም የአንድ ሀገር ልጆች ሊከፋፈሉ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ከበጎቹ ባሱ ግልገሎቹ የሚለውን አባባል በራስ ላይ ከመጋበዝ ባሻገር የሕዝብን የትኩረት አቅጣጫ ለማሳትና ለማዘናጋት፣ከዛም አልፎ ለወደፊቱ አደገኛና በቀላሉ ሊበርድ ወይም ሊጠፋ የማይችል እሳት በወንድማማቾች መካከል መለኮስ መሆኑን መናገር ነቢይ መሆንን አይጠይቅምና በዚህ አደገኛ አዝማሚያ ባለው አካሄድ ዙሪያ ያሉ ሁሉ ከወዲሁ ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ ቢያስቡበት ቢመክሩበትና ከሁሉም በላይ ለሁላችንም የጋራ ለሆነው ፅንሰ ሃሳብ ማለትም ለኢትዮጵያዊነት ቅድሚያ ሰጥተን ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ ወቅቱ፣ሀገራችንና ወገኖቻችን ከእኛ የሚጠብቁት ተስፋ ሰጪ እውነታ ስለሆነ፣ይህንን በተግባር ለመግለፅ እንችል ዘንድ የኢትዮጵያ አምላክ ይርዳን።